# አማራማ ነኝ!

ምነው አገሩ ፈራ እጅግ ተሸማቀቀ

ተናወጠ ተሸበረ የሸረኛው ልብ ወደቀ።

ስደት ለምን መታሰር ያለጥፋት ያለ በደል፣

ሞትም ቢቃ በማንነት መወርወር ወደ ገደል

ባልኩ ነጻነቴን ለማስጠበቅ እንቅስቃሴ ብጀምር

ለትእግስትም መጠን አለው ይሰጥ ለሰውነቴ ክብር

በተንኮልና በሸንገላ በውሸት በተገመደ ቅንብር

ለጠላቶቼ ህልውና ታሪክ ሲለወጥ ሲበረዝ ክፋት ሲንር

በቃ አልፈልግም ይቁም በሬ ወለደ ውሸታች ሁ

ማንነቴን አስከብራለሁ እኩልነቴን አሳያለሁ

ስላልኩ አገር ተሸበረ ተንጫጫ እንደተልባ

አማራነቴን ለማስካድ ምክር ከጫፍ ጫፍ አስተጋባ

" አንተማ እንደዚህ ሆነህ አልኖርክም

በጠባብነት በጎሰኝነት በነገድህ አትታውቅም

ኢትዮጵያዊ በመሆንህ አማራ ልትሆን አትችልም

ተው ይቅርብህ አትመለስ የያዝከው መንገድ አይበጅህም "

ብለው መከሩኝ አዛኝ ቅቤ አንጓች ጓዶቼ

ነገሩን ሁሉ እንድተው አማራነቴን ረስቼ።

በፍርሃት ርደው አነሳሴን ስለሚያውቁት

በግለቴ በቁጣየ ማቀዝቀዣ ሊደፉበት

አማራነቴን ማንነቴን እያወቁት

ግንባሬን መስጠት እንጅ እንደማልመለስ ለጠላት

ግቤን ሳልፈጽም ያሰብኩትን ሳላደርግ

ሞት ቢመጣ ሁሉም ከቦታው ቢጠረግ

ቆራጥነቴ ጀግንነቴ የሚሻር መስሏቸው በትእግስቴ

አሁን ገና ታያቸው መሰል አገሬን ማቆም መገንባቴ

ኢትዮጵያዊ ነህ ማለታቸው አስገረመኝ ድፍረታቸው

ለቀባሪው አረዱት እንዲሉ ነው እውቀታቸው

ወይ ተንኮል ነው ከጀርባ ያለው ከምክራቸው

ያንስብሃል አማራ አትሁን ማለታቸው

ማንነቴን ሳላስከብር ጠላቴንም ሳልበቀል

ወደ ኋላ እንደማልዞር በሃሰትም እንደማልምል

እያወቁ  ተው አማራ መሆን ይቅርብህ ማለታቸው

ግዝፎ ታየኝ  ንቀታቸው ድፍረታቸው ተንኮላቸው

አማራማ ነኝ ቢመራቸው ቢያቅራቸው ባይመቻቸው

ከንቱነቱን ይወቁት ኢትዮጵያዊነቴንም መጠርጠራቸው

አማራማ ነኝ መቼ ተቀይሬ መቼስ ራሰን ክጄ

ሁሉንም የምቀበል የማበላ የማሳርፍ በደጄ

ካለኝ የማካፍል ፍትህ ላጣ ተቆርቋሪ

የታመመን የምጠይቅ የማዝን ለታሳሪ

ሰው ሲደክም የማግዝ ከሞተም ደግሞ ቀባሪ

እኩልነትን የምወድ አድሏዊነትን አባራሪ

ሃሰትን የምጠላ ሌብነትን የምጸየፍ

በጽናት የምቆም እንጅ በስሜት የማልንሳፈፍ

እንደማሸንፍ ጠልቶቼ የተረዱኝ ደጋግመውም የሚያውቁኝ

ኢትዮጵያየም በደሜ ያለች የአማራ ልጅ አማራ ነኝ